# ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ. ም በኢትዮጵያ ስለተኪያሄደው ምርጫ መታሰቢያ በዳላስና ፎርትዎርዝ የተካሄደው ሕዘባዊ ስብሰባ የጋራ መግለጫ

በዳለስና ፎርትዎርዝ አካባቢ የምንገኝ የተቃዋሚ ኃይሎች፡ የማህበራዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁም ሀገር ወዳድ ግለሰቦች ግንቦት 9 ቀን 2000 ዓ ም በራድሰን ሆቴል ተሰብስበን በምርጫ 97 26 ሚሊየን ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ በነፍስ ወከፍ ፍላጎቱን በማያሻማ ሁኔታ በመግለጹ ጨካኙ የወያኔ አምባ ገነናዊ መንግሥት አገዛዙን ከዳር እስከ ዳር ሕዝቡ እንዳልተቀበለው ሲያውቅ፣

1. ሕዝቡን አረመኔያዊና ፍጹም ዘግናኝ በሆኑ ግድያዎች፣ድብደባዎች፣ ለአስከፊ እስራትና ስደቶች መዳረጉን የሚያስረዳ በማስረጃ የተደገፈ ጥናታዊ ጽሁፍ፣
2. እድገት አሳይቶአል እየተባለ መሰረተ ቢስ ውዳሴ የሚሰበክለት በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ያለው ቅጥ የለሽ የኢኮኖሚ ሂደት ከምን ጊዜውም የከፋና ሃገሪቱን ለጥፋት፣ ሕዝቧን ለከፋ የኑሮ ውድነት፣ለረሃብና ለሰቀቀን እየዳረገ መሆኑን፣
3. የጊዜውን የፖለቲካ ብልሹነትና ስርአት ያጣ የአስተዳደር ገጽታ ለማረም ምን ማድረግ እንደሚበጅ የሚያመላክቱ አስተያየቶችን፣
4. እንደለመደው የኢትዮጵያን መሬት ለባእዳን አሳልፎ ለመስጠት በሱዳን ድንበር ወያኔ የሚወሰደውን እርምጃና በመሬቱም ላይ ሰፍረው ባሉት ኢትዮጵያውያን/ት ላይ የሱዳንና የኢትዮጵያ መንግስታት የሚያደርሱትን የጭካኔ በደል የሚያስረዳ ዘገባ ቀርቦልን አድምጠናል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትንና በአጠቃላይ ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በአገራችንና በወገኖቻችን ላይ የሚያደርሰወን ሥር የሰደደና ዘርፈ ብዙ የመብት ረገጣ፣ የብዝበዛ፣ ሕዝብን የመከፋፈል፣ ሉአላዊነትን የማስደፈርና የማን አለብኝነት በደል በቁጭት ገምግመን ከተወያየን በኋላ ጉባኤው የሚከተለውን የጋራ መግለጫ አውጥቷል፡፡

1ኛ ካለምንም ማወላዳት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበር፣ ለዲሞክራሲ፣ ለፍትህና ለነጻነት ሲታገሉ የወደቁትን ወገኖቻችንን አርማ አንስተን የግንቦት 97ን መንፈስ በማስታወስ ትግሉን ከፍጻሜ ለማድረስ ቃል ኪዳናችንን እናድሳለን፡፡

2ኛ በታሪክ የተገነባውንና ለዘመናት ተሳስቦና ተከባብሮ የሚኖረውን ሕዝብ አንድነት ለመበታተንና ከፋፍሎም ለመግዛት የአምባ ገነኑ የወያኔ መንግስት የሚጠቀምበትን በዘር፣ በሃይማኖት በጎሳ በክልልና በቀዬ የመከፋፈሉን መርሆ አጥብቀን እንቃወማለን፡፡ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከጎናችን እንዲቆም እንጠይቃለን፡፡

3ኛ በጥቅም፣ በቁራሽ መሬትና በተለያዩ የድለላ ዘዴዎች በውጭ ያለውን የተጠናከረ የተቃዋሚ ኃይል ለመከፋፈል የሚሯሯጡትን ሰርጎ ገብ የወያኔ ካድሬዎች አተኩሮ በመመልከትና በንቃት በመከታተል ከመሃሉ እየመነጠረ እንዲያወጣቸው እየጠየቅን እኩይ ሥራቸውንም አጥብቀን እናወግዛለን፡፡

4ኛ የአባቶቻችን ደም የፈሰሰበትን አጥንታቸው የተከሰከሰበትን የኢትዮጵያን መሬት ዛሬ አምባ ገነኑ የወያኔ መንግስት ከህዝብ በስተ ጀርባ በተሰወረ ደባው በጀግኖች ልጆቿ ተከብሮ የኖረውን ዳር ድንበር እንደ ገና ዳቦ እየቆራረሰ ለባዕዳን መስጠቱን አጥብቀን እንቃወማለን፤ እናወግዛለን፡፡ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ላለማስደፈር ከሚታገሉ ወገኖች ጋር በቆራጥነትና በአጋርነት እንቆማለን፡፡

5ኛ የውጭ አገር መንግሥታት በተለይ ኃያላኑ አሜሪካና እንግሊዝ በጊዜአዊ ጥቅምና የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመደለል ሕዝብ ያልመረጠውንና ያልወከለውን አምባገነን መንግሥት እየደገፉ የስልጣን እድሜውን በማራዘም የጥፋቱ ተባባሪ መሆናቸውን

አጥብቀን እንቃወማለን። ይልቁንም ለዘላቂ የጋራ ዕድገትና ሰላም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆሙ ጥሪ እናቀርባለን።

6ኛ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጫንቃው ላይ ከተጫነበት አምባ ገነናዊ አገዛዝ ነጻ ማውጣት አማራጭ የሌለው የዜግነት ግዴታ ስለሆነ የተቃዋሚ ኃይሎች፣ ሕዝባዊና ማህበራዊ ድርጅቶች እንዲሁም በግላችሁ የምትንቀሳቀሱ አገር ወዳዶች ልዩነታችንን ወደጎን በመተው በከፍተኛ መቻቻልና መግባባት በአንድነት ቆመን ከጫንቃችን አውርደን እንድንጥል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ. ም በኢትዮጵያ
ስለተኪያሄደው የሕዝባዊ ምርጫ መታሰቢያ
የተከናወነው ጉባኤ

ዳላስ ቴክሳስ ግንቦት 9 ቀን 2000 ዓ. ም